# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 30/2002 ዓ.ም

## ይድረስ ለላብ አደሩና ለሰርቶ አደሩ!!

በ2005 ዓ.ም. በተደረገው ሕዝባዊ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዳር እስከዳር በነቂስ ወጥቶ በምርጫ ካርዱ የመለስ አገዛዝን ከሥልጣን ባስወገደበት፤ የዓለምን ሕዝብ ሳይቀር ባስደነቀ የትግል ተሳትፎ የናንተ የላብ አደሩና የሠርቶ አደሩ አቢይ ሚና በታሪክ የተመዘገበ ነውና ማንም ከቶ ሊፍቀው የሚችል አይደለም። ቀደም ብሎም ቢሆን ለዓመታት ባካሄዳችሁት መራራ ትግል በተለይም ደግሞ ኢሠአማን በወቅቱ ለማቋቋምና ለማጠናከር ከነአበራ ገሙ፣ ዳሮ ነጋሽ፣ እስከነማርቆስ ሀጎስ ድረስ ያደረጋችሁት የትግልና የመስዋዕት ጉዞ የእድሜ ባለፀጋ ለመሆን ለታደሉትና መመስከር ለሚችሉት የትግል አጋሮቻችሁ ሁሉ ከንዳቸውን እስከሚንተራሱ ድረስ የሚረሱት ሳይሆን ተንከባክበው ለወጣቱ ትውልድ በቅርስነት የሚያስተላልፉት ለመሆኑ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ከኢሕአፓ ጎን በመሰለፍም ላብ አደሩና ሠርቶ አደሩ ለመብቶቻችሁና ለሀገራችሁ ያደረጋችኋቸው መራራ ትግልም በሀገራችን ታሪክ ክቡር ቦታን ይዞ ይገኛል። ይሁንናም በየረድፉ፣ በየወቅቱ፣ ከፍተኛ መስዋዕት ብትከፍሉም የትግላችሁን ፍሬ በመልክ ቢለያዩም በይዘት ግን ተመሳሳይነት ባላቸው አምባገነኖች ተነጥቃችሁ መበደላችሁ፤ መጨቆናችሁ፤ በመብት አለመከበርና በመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳ ስቃያችሁ እስካሁን ድረስ ቀጥሎ ይገኛል።

ሁላችሁም እንደምታውቁት የወያኔ ቡድን ለሥልጣን ከበቃ ከ18 ዓመታት ጀምሮ የጥፋት ተልዕኮውን፡ የመብት ረገጣውን በናንተ ላይ ያነጣጠረ ለመሆኑ ከበቂም በላይ በራሱ ድርጊቶች አረጋግጦላችኋል። በርካታ አባሎቻችሁንና ደጋፊዎቻችሁን አፍኖ አስሯል። ቁጥራቸው በጉልህ ያልታወቁትን ገድሏል። ደብዛቸውን አጥፍቷል።አሁንም በዚሁ የጥፋት ጎዳናው ለመቀጠል እየጣረ መሆኑን በገሀድ የምታዩት ነው።

- ወያኔ የመደራጀት ነፃነታችሁንና ጥቅማችሁን የማስጠበቅ መብታችሁን ገፎ በሱ ትዕዛዝ ብቻ የሚንቀሳቀሱ ተለጣፊዎች አቋቁሞ ከአሰሪዎቻችሁ ጋር የመደራደር ኃይላችሁን ክፉኛ አዳክሞባችኋል። ራሳችሁን ከብዝበዛ የምትከላከሉበት ሕግና መብት ነፍጓችኋል። በሀገራችሁ በፈለጋችሁበት አካባቢ ሠርቶ የማደር ብቻ ሳይሆን ሥራውንም የማግኘት እድሉን እንኳ በዘርና በክልል ገመድ አጥሮባችኋል። አለአግባብ ከሥራ መባረርና ከቁያችሁ መፈናቀል የእለት ጉርሳችሁ መሆኑን የምታውቁት ነው።
- መደባዊ አንድነታችሁን እንዳታረጋግጡ በብሄረሰብ ደረጃ በመከፋፈል ከፍተኛ ጋሬጣ ደቅኖባችኋል። የዚህ መሰሪ የሆነ ድርጊቱ ዋና አላማው እናንተን ረግጦና ተቆጣጥሮ ለመግዛት እንዲያስችለው እንደሆነም በግልጽ የምትረዱት ነው። ለዚህም ነው ወያኔ ሥልጣን ሲጨብጥ የመጀመሪያው ተግባሩ የነበረው በትግላችሁ አምጣችሁ የወለዳችሁትን መኢሠማን ያገደባችሁ።

ከዛም በሀገር አቀፍ ደረጃ ራሳችሁን አዋቅራችሁ ኢሠማኮን አደራጅታችሁ ጥቅማችሁን ለማስከበር ያደረጋችሁት ሙከራም መሪዎቻችሁን በማዋከብ፡ በመወንጀልና በማሰር ብሎም ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ በማድረግ የድርጅታችሁንም ንብረት በመዝረፍ ተለጣፊ ድርጅት መስርቶባችሁ ድርጅትና ትግል አልባ እንድትሆኑ አድርጓችኋል።

አሉ የሚባሉ ኩባንያዎችንና ኢንዱስትሪዎችን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለስንት ወራት ያለ ደሞዝ ሲገለገልባችሁ እንደነበር፡ ያለምንም ዋስትና አውላላ ሜዳ ላይ የጣላችሁንም በሀዘኔታና በቁጭት እኛም፡ እናንተም የምናስታውሰው ነው። "በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ" ሳቢያ ለሱ ታማኝ ያልሆናችሁትና ማንነታችሁን አስከብራችሁና አስጠብቃችሁ፡ ጥራችሁ፡ ግራችሁ ኑሯችሁን ለመምራት የፈለጋችሁትን ደግሞ ከሥራ ባልደረቦቻችሁ ለይቶና መንጥሮ አባሯችኋል። በኑሮ ውድነቱ እየደረሰባችሁ ያለው ሰቆቃ እግዚዖ የሚያሰኝ ነው። ለሥራችሁ የሚደረግላችሁ ክፍያ ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ቤተሰቦቻችሁ ጠግበው ለማደር፤ ለሰውነት መሸፈኛ የሚሆን ልብስ መግዣ፤ የጤና ጉድለት ሲደርስ ለማሳከሚያ፤ ልጆቻችሁን በትምህርት አንጾ ለማሳደጊያ በቂ ባለመሆኑ ምክንያት ከድህነት ወለል በታች ለመኖር የተገደዳችሁ ቁጥራችሁ በርካታ ነው። የአገዛዙ ደጋፊ አይደላችሁም ተብላችሁ የምትጠረጠሩ ሁሉ በየጊዜው በሚደረግ ግመገማ ሳቢያ የምትመነጠሩትም ለናንተ ግልጽ ነው።

በመሆኑም ሰብዓዊ መብቶቻችሁ ካልተከበሩ፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችሁን በቆራጥ ትግላችሁ ካልተጎናፀፋችሁ የድካማችሁን ፍሬ ሁሌም እየተነጠቃችሁ ለጭፍን ብዝበዛ መዳረጋችሁና በድህነት እሳት መጠበሳችሁ የማይቀር መሆኑን ከናንተ በላይ ሊያውቅ የሚችል የለም። በተገኘው መልካም አጋጣሚ ሁሉ በልዩ ልዩ የትግል ሁኔታዎችን በመጠቀም ድምፃችሁን ብታሰሙም፤ ምርጫችሁን ብትገልጹም ድምፃችሁ ተቀምቶ ታሰራችሁ ተፈጃችሁ እንጂ ያተረፋችሁት ለውጥ ከቶም የለም። ታዲያ ኑሯችሁ ብዙም ሳይሻሻል፤ ፍትህን ሳታገኙ፤ በበሽታ እየተጠቃችሁ፤ በድህነት እየተቆራመዳችሁ ካለ እድሜ እየረገፋችሁ በደልን መሸከማችሁ ለአንዴም ለሁሌም ሊያከትም ይገባል እንላለን። ስለዚህም በቃ ማለት ሲያንስ ነው። ለዚህም ከበቂም በቂ ምክንያቶች አሉ።

ለዓመታት ትግል ያካሄዳችሁባቸው የኤኮኖሚና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ያልተመለሱ በመሆናቸው አሁንም ሕያው ናቸው። ተገኘ ከሚባለው የኤኮኖሚ እድገት ለናንተ ጠብ ያለላችሁ ምንም ነገር የለም። እነሱ ስለተረፋቸው እናንተም እንዳለፈላችሁ ሲናገሩ የማሰብና የማመዛዝን ችሎታችሁን መናቃቸውን የሚያመልክት እንጂ ሌላ አይደለም። ወያኔ በሥልጣን ዘመኑ ያካሄዳቸው ክልላዊና ሀገራዊ ምርጫዎችም የራሱን አገዛዝ አጠናከረበት እንጂ ለናንተ የተገኘ ውጤት አለመኖሩንም የምታዩትና የምትኖሩት ነው። እናንተ



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

የኤኮኖሚው አንዱ የጀርባ አጥንት ሆናችሁ ሳለ ባልተካፈላችሁበት፡ ይሁንታችሁን ልትሰጡ በማይፈለግበት፤ በደፈናው አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ ዴሞክራሲ በሚል ስታሊናዊ ፕሮፓጋንዳ እያደነቆራችሁ በሥልጣን ለመቀጠል ያለውን ምኞት፣ ምኞት ሆኖ እንዲቀር ለማድረግ የናንተ ድርሻ ከፍተኛ ነው። ለመለስ አገዛዝ ምርጫ ማጣፈጪያ ሊያደርጓችሁ ከሚጥሩት ገሸሽ ብላችሁ ዘላቂ ጥቅማችሁን ሊያስጠብቅ በሚያስችል ትግል እንድትሰማሩ ኢሕአፓ የትግል ጥሪውን ያቅርብላችኋል። በቅርብ ጊዜ ሊጠናቀቅ የሚጠበቀውና ከሕዝብና ከናንተ አንፃር ሲገመገም ውጤት አልባ ሊሆን በሚችል የምርጫ ቀልድ ተካፋይ እንድትሆኑ የሚደረግባችሁ ጫናም አሁን ያለው ሁናቴ እንዲቀጥል ፍቃድ እንድትሰጡት የሚጠይቅ ከመሆን በቀር በሌላ በምንም አይተረጎምም። ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ከቀጠለ ድህነትንና መብት አልባነትን በውርስ መልክ ለልጆቻችሁ ማስተላለፋችሁ የማይቀር እንደሆነም በሚገባ የምትገነዘቡት ነው። ይህ ደግሞ ከሰብዓዊነት ውጪና ርህራሄነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን ፈጣሪም የማይቀበለው በመሆኑ ተወግዞ ሥርዓቱ ከነአራማጆቹ ሊወገድ የሚገባው ነው። ስለሆነም ፍላጎታችሁ ይሳካ ዘንድ ትግላችሁን ከማጧጧፍ በስተቀር ሌላ መፍትሄ እንደሌለ ኢሕአፓ በጽኑ ያምናል። ይህን እሽ አትበሉኝ ባይ አገዛዝን ከጫንቃችሁ ላይ ማውረድ፤ ሥርዓቱንም እንዲያከትም ማረግ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፉት ሳይሆን በኛው በአሁኑ ትውልድ ስኬታማ መሆን የሚገባው ሀገራዊ ግዴታም ነው። ከምጣዱ ማጥገቡ የሚያስታውቅ ፖለቲካና ትግል ነጥሮ መውጣትና የሁሉንም ልብ መኮርኮር ያለበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው ብንል ከውነት መራቅ አይሆንም።

እናንተ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላችሁ ቁልፍ ቦታ የታወቀ፤ ይህንንም በግንባር ቀደም ትግላችሁ ያስመሰከራችሁ ናችሁ። ባለፉት ጊዜያት ባደረጋችኋቸው ሰላማዊ ሰልፎች፤ የሥራ ማቆም አድማዎች እስከአፍንጫው ድረስ የታጠቀ አገዛዝን ለማርበድበድ፤ ለማድከምና ለመገርሰስ የሚችል ችሎታ እንዳላችሁ የምናወቀውና የምንኮራበትም ነው። ከጥቂት ጊዜያት በፊት በድሬዳዋ የምድር ባቡር ላባደሮችና ሠራተኞች ያደረጉት ትግል በምሳሌነታችሁና በህዋሪያነታችሁ ሊጠቀስ የሚችል ነው። ለዚህም ነው በነጻ ድርጅታችሁ በመደራጀት ከታገላችሁ ምን ውጤት እንደምታስገኙ የሚያውቀው የመለስ አገዛዝ ይህንን ችሎታችሁን ስለሚፈራም ነውና ባለው አቅሙ ሁሉ ለማዳከምና ለመከፋፈል መጣሩ ይህን ጥረቱን ማክሸፍ ከናንተ በተለይ የሚጠበቅ ነው።

ስለሆነም ምን ማድረግ አለብን ለሚለው ኢሕአፓ በተለያዩ መጣጥፎቹና በተለያዩ ጊዜያት በፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዮ ስርጭቱ ግልጽና ይፋ አድርጓቸዋል። በቅርበት ከምትገናኙት ጋር በነዚሁ ላይ በመወያየት ከሁኔታዎች ጋር አስማምታችሁ ተግባራዊ ብታደርጓቸው የስቃያችሁ ዘመን እንደሚያጥር በርግጠኝነት መናገር የሚቻል ነው። በዚህም አዲስ የትግልና የጀግንነት ታሪክም እንደምታስመዘግቡ ኢሕአፓ ጽኑ እምነት



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

አለው። የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖችን አላማ ከዳር ለማድረስም ሆነ ወንዝ የማያሻግር ተስፋ መጃጃሉ የሚያዋጣ እንዳልሆነ በቂ ተመክሮን የገበያችሁ ናችሁ። በነጻ የመደራጀት መብት ተነፍጓችሁና ለጭፍን ብዝበዛ ተጋልጣችሁ በኑሮ ውድነቱና በአገዛዙ ጭካኔ እየተሰቃያችሁ ባላችሁበት፤ ውጤት አልባ ለሆነ ለመለስ የምርጫ ቀልድ ተካፋይ መሆን የሚመረጥ ሳይሆን የሚወገዝና የወደፊት እጣ ፈንታን በራስ እጅ ለማስገባት ወሳኝ ትግል ማድረግ የሚጠበቅበት ወቅት ነው። ኢሕአፓ ምንጊዜም ከናንተው ጎን ነው።

የላብ አደሩ፣ የሥርቶ አደሩ በነጻ የመደራጀት መብት ይከበር!
በትግላችሁ ድልን ትቀዳጃላችሁ!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France